# በእግዚአብሔር ይቅር የተባለ

GOSPEL 316

***«መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣ እንዴት ቡሩክ ነው!» መዝሙር 32:1***

የምናደርጋቸው የተሳሳቱ ነገሮች (በመፅሐፍ ቅዱስ ኃጢአት ተብለው የሚጠሩት) ከእግዚአብሔር ይነጥሉናል። ለዘለዓለም ህይወት ዝግጁ እንድንሆን ... ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማት በእግዚአብሔር ይቅርታ ሊደረግልን ይገባል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ እግዚአብሔር እነዚያን ኃጢአቶች እንዳልነበሩ አድርጎ በቸልታ በማለፍ የእነዚያን ኃጢአቶች ዘላለማዊ ቅጣት እንደሚያስወግድ እየተናገረ አይደለም። ፈጽሞ፣ ቅጣቱ መከፈል አለበት። የምሥራቹ (ወንጌል) ማለት ኢየሱስ [ኃጢአት የሌለበት አምላክ-ሰው የሆነው] በመስቀል ላይ በመሞት ያንን ቅጣት በደሙ አስቀድሞ እንደከፈለልህ የሚናገር ነው። በሌላ አገላለፅ፣ የአንተን ቦታ ወስዶልሃል። ኢየሱስ የአንተ የመስዋዕትነት ምትክ ሆነ። ያ ግን በቂ አይደለም። ያ ክፍያ በአንተ ላይ ተግባራዊ መሆን አለበት ... ወደ ህይወትህ መምጣት አለበት። ወሳኙ ጥያቄ፣ ይህ የሚሆነው እንዴት ነው? ይህም ንስሀ ስትገባ (ከኃጢያትህ ወደ እግዚአብሔር ስትመለስ) እና በጌታ ኢየሱስ ስታምን ይከሰታል። እና ከዚያ፣ እና ከዚያ በኋላ ብቻ፣ በእግዚአብሔር ይቅር ትባላለህ።

## ችግራችን ... መነጠል

*«ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል።»* ሮሜ 3:23

*«ነገር ግን በደላችሁ ከአምላካችሁ ለይቷችኋል፤ ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፤ በዚህም ምክንያት አይሰማም።»* ኢሳይያስ 59:2

*«በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችንም ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል። እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ።»* 2 ተሰሎንቄ 1:8-9

*«የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው።»* ሮሜ 6:23

*«ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣ ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቷልና።»* ሮሜ 5:6

## የእግዚአብሔር መፍትሄ ... ምትክ መሆን

*«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥድረስ ዓለምን እንዲሁ ወድዷልና።»* ዮሐንስ 3:16

*«ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ [የበቃ መስዋዕት] ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው።»* 1 ዮሐንስ 4:10

*«ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል።»* ሮሜ 5:8

*«ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል እናንተ ተፈውሳችኋል።»* 1 ጴጥሮስ 2:24

*«ለተቀበሉትና [ኢየሱስ] በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው።»* ዮሐንስ 1:12

## የይቅርታ መንገድህ ... በጌታ ኢየሱስ ማመን

*«በእርሱም [ኢየሱስ] የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።»* ሐዋርያት ሥራ 10:43። *«በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ዓማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤»* ኤፌሶን 2:8-9። በንስሐ ... ማለትም፣ በእምነት ወደ ኢየሱስ በመመለስ በኢየሱስ ማመን ትችላለህ (ስለ ማመን ብቻ አይደለም)። ይህ ጸሎት ለእናንተ ያንን የምታደርግበት መንገድ ነው። ይህ መሐላ ወይም የምትሃት ቃል አይደለም። በእውነት የልብህ መሻት ከሆነ ጸልይበት።

**ውድ እግዚአብሔር ሆይ፣**
**ፍላጎቴን አውቃለሁ ... ኃጢአተኛ ነኝ።**
**ንስሃ እገባለሁ ... ከኃጢአቴ ወደ አንተ እመለሳለሁኝ።**
**በኢየሱስ ... አምላክ በመሆኑ ለእኔ በመስቀል ላይ እንደሞተ አምናለሁ።**
**አዳኜ እንዲሆን እጋብዘዋለሁ።**
**አሜን**

ኢየሱስ የኃጢያትህን ቅጣት ከፍሏል። እና በኢየሱስ በማመን፣ ክፍያው የአንተ ክፍያ ሆኗል።
በእግዚአብሔር ይቅር ተብለሃል። ኢየሱስም ለዘላለም ደህና እንደሆንክ በዮሐ 3፡16 ላይ ተናግሯል።



***«መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣ እንዴት ቡሩክ ነው!» መዝሙር 32:1***

*በእግዚአብሔር ይቅር የተባለ ነፃ ፒዲኤፎች በበርካታ ቋንቋዎች ከ* Gospel316.org *የተገኙ ናቸው።*

**ያንን ጸሎት ከልብህ ከጸለይክ፣** በእግዚአብሔር ይቅር ተብለሃል እናም ከእርሱ ጋር ለዘላለም ትስማማለህ። የኢየሱስ መስዋዕታዊ ሞት ይቅርታን ሰጥቶሃል። እግዚአብሔር አሁን ርስት ሆነህ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ... ለፍርድ እንደማትቀርብ ... እና ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርክ ተስፋ ሰጥቶሃል፣ ዮሐ 5፡24። ከኃይለኛው እጁ ማንም ሊነጥቅህ ስለማይችል ደህንነትህ የተጠበቀ ነው። እርሱን አጥብቀህ ከምትይዘው ይልቅ አንተን አጥብቆ ይዞሃል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ *«እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም። እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም፣»* ዮሐንስ 10:28-29።

**ያንን ጸሎት ለመፀለይ ዝግጁ ካልሆንክ፣** *መፀለዩን ቅድሚያ የምትሰጠውን ነገር አድርግ። ውሳኔህ ዘላለማዊ ጠቀሜታ እና ውጤት ነው። ከመቃብር በኋላ ሁለተኛ እድል የሚባል ነገር የለም፣ «ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል፣»* ዕብራውያን 9:27። ውሳኔንህ ላይ የሚቆሙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ካሉህ ይህን የሰጠህን ሰው አነጋግር።

## ምሳሌዎችና ፍቺዎች

**ይቅርታ።**
ይቅርታ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ለኃጢአታችን ቅጣት ክፍያን ይጠይቃል። የኃጢአት ቅጣትም ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ማለት ኃጢአትህን እና ቅጣቱን ካንተ ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እና ቅጣቱን ኃጢአት በሌለበት ኢየሱስ ላይ አኖረ። ከዚያም እግዚአብሔር የራሱን ጽድቅ ሰጠን። በመንግስተ ሰማያት ውስጥ እንዳሉት ሁለት መጻሕፍት ነው። የመጀመሪያው፣ የመመዝገቢያ ደብተርህ፣ ለፈፀምካቸው ስህተቶች ሁሉ ምልክት አለው። ገፆቹ በምልክቶች ተሸፍነዋል። የምናደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ኃጢአት (የድርጊት ኃጢአት) እና አንዳንድ የማናደርጋቸው ነገሮች ኃጢአት (የውርስ ኃጢአት) እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። አንዳንድ ሐሳቦች እንኳን ኃጢአተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። በቀን ሦስት ኃጢአቶች በየዓመት 1,000 ይሆናል። በሕይወት ዘመን ሁሉ ሲሆኑ፣ ያ ብዙ ኃጢአቶች ናቸው። ሌላኛው መጽሐፍ ኃጢአት የሌለበት የኢየሱስ የመዝገብ መጽሐፍ ነው። ገጾቹ ንጹህና እንከን የለሽ ናቸው። በኢየሱስ ስታምን፣ ይህ በሁለቱ መጽሐፎች ላይ ያለው ሽፋን የተለዋወጠ ያህል ነው። ከዚያ ስምህ ያለበት የመዝገብ ደብተር ሙሉ በሙሉ ንጹህ ነው። ኃጢአትህና ቅጣቱ አልፏል።

**እውነተኛ መፍትሄ።**
ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ *«ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፣»* ዮሐንስ 14:6። በኃጢአት የተነሳ ከእግዚአብሔር ለመነጠላችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው መፍትሔ ልዩ ነው። ሌሎች ሐይማኖቶች ከኃጢአታችን ጋር ለዘላለም መጋፈጥ ፈልገን በዚያ ሊኖር የሚችል ማንኛውም ኃጢአታችንን የሚረሳ አምላክ ተስፋ በማድረግ እንድንኖር ይጠይቁናል። የኢየሱስ መንገድ ሐጢያታችንን በማስተሰረይ ... በማጠብ ረገድ ልዩ ነው። ከዚያም ኃጢአታችን ተሰርዞ በኢየሱስ ላይ ተላልፏልና እግዚአብሔርን እና ዘላለማዊ ህይወትን እናገኛለን። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ፃፈ፣ *«መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና፣»* ሐዋርያት ሥራ 4:12። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ፃፈ፣ *«አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል፣»* 1 ጢሞቴዎስ 2:5-6። የኢየሱስ መንገድ እውነተኛ መፍትሄ ነው።

**በኢየሱስ ማመን።**
ኢየሱስን ማመን ስለ ኢየሱስ ከ*ማመን* በላይ ነው። በድንገት ሞተሮቹ መበላሸት ሲጀምሩ ከተራራው በላይ ከፍ ብሎ የሚበር የአውሮፕላን ውስጥ ተሳፋሪ እንደሆንክ አድርገህ አስብ። አውሮፕላኑ ወደ ከባድ የመከስከስ አደጋ እየወረደ ነው። የአውሮፕላኑ አብራሪ ሁሉም ሰው ፓራሹቱን ታጥቆ በተከፈተው በር ከአውሮፕላኑ እንዲዘል አዘዘ። ስለ ፓራሹት ታውቃለህ። በቴሌቪዥን ላይ አይተሃቸዋል። አሁን ግን የተለየ ነው። ከዚያ አይሮፕላን ክፍት በር ለመዝለል ስለ ፓራሹት ከ *ማመን* በላይ በፓራሹቱ ላይ *ማመን* ይፈልጋል ... እናም አንዳንድ የእግረኞች ቦርሳ አይሰራም። ህልውናህ ትክክለኛውን ፓራሹት ይፈልጋል ... ያለ እሱ መዝለል እርግጠኛ ሞት የሚያስከትል ነው። በፓራሹት መዝለል 100% የእምነት ቃል ኪዳን የሚያሳይ ነው። አንዳንድ ጥርጣሬዎች ሊኖርህ ይችላሉ ... ግን ለመዳን ሙሉ እምነትህን በፓራሹቱ ላይ ማድረግ ያስፈልግሃል። ኢየሱስ እውነተኛው ዘላለማዊ ፓራሹት ነው። በእምነት ውጣ። በእርሱ እመን!

**የሕትመት መመሪያዎች።** በአንድ ገጽ ላይ በሁለቱም ጎን ማተም ይመከራል። በከለር ወይም በጥቁርና ነጭ ያትሙ።

---

*በእግዚአብሔር ይቅር የተባለ* © 2024 በ Acts One Eight የታተመ ሲሆን ከ www.Gospel316.org የተገኘ ነው። ይህን ሙሉ መግለጫ በማካተት ይዘቱን ሳትለውጥ በነጻነት ማተም፣ መቅዳት፣ መለጠፍ ወይም መላክ ትችላለህ። ይሁንና፣ የሚኒስትሪህን ወይም የቤተክርስቲያንህን ስም ወይም አርማ ልታክልበት ትችላለህ። Acts One Eight የተመሰረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው። ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑና ከዚያም የእርሱ ደቀ መዛሙርት ወደመሆን የሚድጉበት እርዳታ አለ። እንግሊዝኛ ላልሆኑ ትርጉሞች የትርጉም አገልግሎቶች የሚቀርቡት በ www.ChristianLingua.com ነው። ከዋናው የእንግሊዝኛ ቅጂ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከአዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (NASB) የተወሰዱ ናቸው። በዚህ እትም ውስጥ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከ «አዲሱ መደበኛ ትርጉም» እትም ነው።